# የቂም ሰብል

የባህሩን ጠረፍ- እንደ ዳቦ ቆርሰው

የምዕራቡን ድንበር - ለባዕድ አውርሰው

መሃሉን ዳር አርገው - ኬላውን አፍርሰው

ስንት አርበኛ ገድለው - ንፁህ ደም አፍስሰው

ድሃውን ገበሬ - አፅሙ-ርስቱን ወርሰው

ከቀየው ፈንግለው - ሚች ርሃብተኛ

አምራቹን አድርገው - ሁሉን ስደተኛ

ህዝቡን ጦም አዳሪ - ተመፅዋች አድርገው

በድህነት ህይዎት - ኩራቱን አዋርደው

ወኔው ተኮላሽቶ - ላገዛዝ እንዲመች

መብቱን አፍነው - አስረው እግር ከወርች

ሥርዓተ-ትምህርቱን -መሠረቱን ንደው

ልሂቁን በነቂስ - ካገር አሰድደው

ተቃዋሚውን ሃይል - እስር ቤት ጎድጉደው

ህዝቡን በዘር ከፍለው - እርስ-በርስ አፋጅተው

ቅራኔውን አርገው - እረቅ የማይፈውሰው

ለልጅ ልጅ የሚተርፍ - ቂም በቀል አውርሰው

ዕረግጠው የገዙት _ ቀንበሩን ሰባብሮ

ሚች ከገዳዩ ጋር - ቦታ ተቀያይሮ

በደም ፍላት ስሜት - ነገ ሲገናኙ

በቂም በቀል ባህር - በደም እንዳይዋኙ

**አረ ተው በሏቸው - እኒያን ሰሜነኞች**

**አያርጉት በደሉን - ለፍርድ እንዳይመች!!!**

**ጥር 2002**

**abraham beyenne**